# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
*Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP)*


የካቲት 30 ቀን 2011 ዓ.ም.

## የአዲስ አበባን ማንነትና ይዞት በመደገፍ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ኢሕአፓ ይደግፋል

እሁድ መጋቢት 1 ቀን 2011 ዓ.ም በአዲስ አበባ በባልደራስ አዳራሽ ስለ አዲስ አበባ ምን ይደረግ በሚል ውይይት የሚደረግ መሆኑን ተገልጿል። ኢሕአፓ ይህን ስብሰባም ሆነ የአዲስ አበባን ማንነትና ይዘን በመደገፍ የሚደረገውን ማንኛውንም እንቅስቃሴ የሚደግፍ መሆኑን ይገልጻል።  በላያችን ላይ በአሜሪካ የተሰየሙብን ሹሞች ዋና ገጽታቸው ዘረኝነትና ጠባብ ወያኔያዊ ግን የኦሮሞ ብሄርተኛነት መሆኑን ስናጋልጥ ቆይተናል ። ኢትዮጵያዊነት ሱሳችን ነው ሲሉ የነበሩት ግለሰቦች ዋና መልእክታቸው ተጨፈኑ እናሞኛችሁ እንጂ በልባቸው ኦሮሚያን ለማስቀደም ቆርጠው መነሳታቸውን ከመጀመሪያው ያጋለጥነው ነው ። ዛሬ በይፋ አዲስ አበባን ለመጠቅለልና የኦሮሞ ነው በማለት የሚንቀሳቀሱት ክፍሎች ቀጥለውም ከድሬ ዳዋ እስከ ወሎ ደረስ ኦሮሚያ ነው በሚል ቅዠት ሕዝብን ሊያፈናቅሉ፤ ሊፈጁና ሊያስፈጁ ተነትሰዋልና ይህንን በመቃወም የሚወሰዱ ሕዝባዊ እርምጃዎችን ሁሉ ኢሕአፓ ሙሉ በሙሉ መደገፉን መግለጽ ይፈልጋል ። ተንጋግተው ወደ አዲስ አበባ የሄዱትና  ተቃዋሚ ድርጅት ነን የሚሉት የፖለቲካ ድርጅቶች ሁሉ ጠባብ ብሄርተኞች ኢትዮጵያ ላይ ጥቃት ሲፈጽሙ እያዩ በለሆሳስም ቢሆን መቃወም አለመቻላቸው ለትዝብት የሚያበቃቸው ከመሆኑ በላይ  ተቃዋሚና  መሆን አቅቷቸው የጠባቦቹ አወዳሽና ተለጣፊ መሆናቸው አሳዛኝ ድርጊት ሆኖ ይገኛል።

ወያኔ የጎንደር የወሎንና  የአፋርን መሬት የትግራይ  ነው ብሎ ጠቅልሎ መያዙ ብቻ ሳይሆን መሬታችንን ለሱዳንም ለሻዕቢያም መስጠቱና መተማ ሳይቀር ትግራይ ነው የሚል ቀረርቶ እያሰማን ነው ። ጠባቦቹና ማፈሪያ ሹሞች ደግም ከድሬዳዋ እስከ ወሎና ብሎም አዲስ አበባ የእኛ ነው  በሚል እየፎከሩብን ነው ። ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን ክደው ሜንጫ ለአማራ ለክርስቲያን ከሚሉት ጋር ገጥመዋል ።መግጠም ብቻ ሳይሆን ዋናው አንቀሳቃሽ ለመሆናቸው የቡራዩን የሕዝብ መፈናቀል ባለስልጣኖቹ ራሳቸው ማዘዛቸውን መረጃው መገኘቱንም ለማወቅ ተችሏል።  አዲስ አበባ ፍንፍኔ ነበረች አሁንም ናት የሚለው አባባል ልብ ወለድ ነው ። የአለውን እወነት ክዶ፤ ማንነትን ክዶ ለመስፋፋት የታሰበው ለከፋ ችግር የሚዳርግ እንጂ እውን የሚሆንም አይደለም ። የሚያመጣው ደም ማፋሰስ እንጂ ግባቸውን ሊያገኙ ከቶም አይችሉም ።ሕዝብን መናቅ መጨረሻው ውድቀት ነው።  ሹሞቹ ኢትዮጵያዊ ሳይሆኑ ጠባብ ጎጠኞች መሆናቸውን በዕብሪት አሳይተውናል ። አዲስ አበባናን ሌሎችን ከተሞችና ጠቅላይ ግዛቶች የእኛ በሚል ጀሌዎቻቸውን አሰባስበው የጀመሩት  ጸረ ሕዝብ ጸረ ኢትዮጵያ ዘመቻ ውድቅ እንደሚሆን ስናረጋግጥ በሙሉ እምነት ነው ። ዋናው ቁም ነገር ግን ሹሞቹ ለኢትዮጵያ ሳይሆን ለጥበትና ዘረኝነት የቆሙ መሆናቸውን ሁሉም ተረድቶ ሊያገላቸው ሊታገላቸው መነሳት እንዳለበት መገንዘቡ ነው ።


**EPRP**
**P.O.BOX  73337**
**Washington DC,  20056**
**USA**

**Email  [ESPIC@aol.com](mailto:ESPIC@aol.com)**
**Website  [www.eprp.com](http://www.eprp.com)**

**EPRP**
**BP  30022**
**92276 Bois Colombes cedex**
**France**

**Tel.  202 291 4217    Fax:  202 291 7645**

አዲስ አበባ የሁሉም ኢትዮጵያዊ እንጂ የማንም ጎጠኛ አይደለችም ። ዘረኛውን ወያኔ ስናዳክም ሌላ ዘረኛ አገዛዝ ሊተካውና ሊያስቀጥለው በአሜሪካና አረቦች ድጋፍ መጥቶብናል ። አውሬ ዘረኞች መድረክ ይዘው ሕዝብን ሊያፋጁና ኢትዮጵያን ሊያጠፉ ተሰልፈዋል ። መድረክ እንዲያገኙ ፈቃድ የሰጧቸው ዘረኞቹ ሹሞች ናቸው-- ግባቸው አንድ ነውና። በዚህ ውርደትና ክህደት አንፈርጅም በማለት ተቃውሞአቸውን የሚያሰሙትን ሁሉ ኢሕ አፓ ድጋፉን ይገልጥላቸዋል ።ተቃውሞው በሁሉም መስክ ይፋፋም።ገንጣይ ጠባቦችን ወደዱም ጠሉም እናቸንፋቸዋለን ።

ጸረ ጠብ ዘረኞች ትግላችን ይፋፋም !!
ሀገር አድን ትግላችን ይፋፋም!!
ኢትዮጵያዊነት ተጠናክሮ የድል ባለቤት ይሁን !!